**ዜና ዘገባ (የካቲት 23፣ 2000 ዓ. ም.)**

**የወያኔው ቀንደኛ የደህንነት ባለስልጣን ሞተ ተባለ፣ በደብረ ዘይት ጉዳይ አገዛዙ ጥርስ ነክሶበት ነበር፣ ህዝቡ በኑሮ ውድነት ሲቸገር ወያኔ ቡችሎቹን በከፍተኛ ወጪ ላንጋኖ ሲያዝናና ዋለ፣ መከላከያ ሚ/ር በውጭ የሚሳኤል ባለሙያ መኮንኖች ተጨናንቋል፣ 2 የዲላ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊሶች ተቀጥቅጠው ተገደሉ፣ የአራት ኪሎ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች ተቃውሞ ቀጠሉ »»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ**............................

የወያኔው ከፍተኛ የደህንነት ሹም በድንገት መሞቱ ታወቀ:: ከእነ ክንፈ ገ/መድህን ጋር ሃገሪቱን ሲያምስ የነበረውና አሁንም ከእነ ጌታቸው አሰፋ ጋር በመሆን ሃገሪቷን እና ሕዝቧን ሲያምስና ሲያመሰቃቅል የነበረው ታሪኩ ሴዶ የተባለው ከፍተኛ የወያኔ ደህንነት ባለስልጣን ሰኞ የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ከደብረዘይት ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ላይ እያለ የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት ሕይወቱ አለፈ ብሎ የተናገረው ደግሞ የተፋውን ምራቅ መልሶ መላስ የሚውቅበትና ገድሎ ሃዘን መቀመጥም ሆነ ማዋየቱን የተካነው ወያኔ ነው ይላል የሪፖርተራችን ዘገባ ከአዲስ አበባ::

ለወያኔ እጅግ ከፍተኛ ስራዎችን ሲሰራላቸው የነበረው ይኸው ታሪኩ ሴዶ የተባለው የደህንነት ሹም ከእነ ጌታቸው አሰፋ ጋር በመሆን በሃገሪቷ የሚከናወኑ ወያኔያዊ የደህንነት ሥራዎችን በከፍተኛ ደረጃ ሲያንቀሳቅስ የነበረና በወያኔው መሪ ኪስ አይገባ ሙገሳ የተቸረው ነበር ይላሉ በቀብሩ ስነስርአት ላይ ቀጨኔ መድሃኒያለም ቤተክርስትያን ዘጋቢያችን ያገኛቸው የደህንነት ሰው

ታሪኩ ሴዶ ሰኞ እለት ጠዋት ወደ ደብረዘይት ተጉዞ ወያኔ ደብረዘይትን ወደ ፌዴራል ስር ለማስገባት ያቀደውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሯሯጠ መዋሉና የደህንነት ስራውንና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን ሲያከናውን ሲባዝን ነበር የዋለው እውነትም አንድ ግዜ ሲጠሩት አስር ግዜ አቤት ለሚልላቸው ለጌቶቹ ወያኔዎች የተሰጥን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ «በሾርኒም» የእነአባ ዱላ ገመዳሶች ስትፋቁ ኦነግ ናችሁ የተባሉትን ሲከታተል መረጃ ሲሰበስብ ውሎ ግዳጁን ተወጥቶ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ እያለ ነው ሂድ ብለው የላኩት አለቆቹ እንደባህላችን በጠዋት ሳይሆን በምሽት «የመኪና አደጋ ደረሰበትና ሞተ»ብለው መርዶ አረዱን

ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ሞት አሳዛኝ ቢሆንም በወያኔዎቹ የማይመስል ምክንያት ግን በመደንገጥ ፈንታ የተገረመው አዲስ አበቤ ብዙ ነው ተብሎዋል

በቅርቡ ደብዘረይት ከተማን ጨምሮ አድኮ፣ ዱከም አቃቂና ሌሎቹንም ከተሞች ከፍተኛ አመታዊ ገቢ ያላቸው ከተሞች በመሆናቸው እና ከዚህ ይበልጥ ደግሞ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የሕወሓት ሰዎች ግዙፍ ካምፓኒዎቻቸው የቆሙት በህዝብ ላብና ወዝ የተገኘጥሬ ሃብት ተዘርፎ ባለሃብት የተሆነበት ከተማ እተመረጠ ለህልውናችን አስፈላጊ እርምጃ ይወሰድለት በማለት በተደጋጋሚ ድርጅታዊ ስብሰባ ላይ የሚነሳውን ማሳሰቢያ መሠረት በማድረግ ቀድሞም ይፈልግ የነበረው የወያኔ ቡድን ከኦሮሚያ ክልል ነጥቆ ወደ ፌደራል ስር ለማስገባት ያቀዳቸውን ስውር እቅዶቹ ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን ዘገባ ስረዳል

ወያኔ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሕዝቡን ስሜት መረዳት በሚል የፍተሻ ስራም የተሰራ ሲሆን በዚህ ወቅትም የደብረዘይት ከተማ ነዋሪዎችና ወጣቶች ጉዳዩን በጭምጭምታ ሰምተው ብጥብጥ ያነሳሉ ተብሎ ከፍተኛ ስጋት አሳድሮባቸው ስለነበር ይህንኑ በመኪና አደጋ ሞተ የተባለውን ታሪኩ ሴዶ ከፍተኛ የደህንነት ባለሥልጣን በቦታው በመቶዎች የሚቆጠሩ የደህንነት ባለሥልጣን ሰራተኞችን አስከትሎ ይህንኑ ጉዳይ እንዲያስተካክል የተደረገ እንደነበረም ከዘገባው ለማወቅ ተችሎዋል።

ይሁን እንጂ ምንም እንኩዋን የወያኔ ቡድን እቅዱን ያጠናቀቀ ቢሆንም በአሁን ሰዓት በመላ ሃገሪቱ ሕዝቦች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ የገባ በመሆኑ በደብረዘይት መገንጠል ምክንያት ሕዝቡ ተቃውሞ ቢያነሳ በሌሎች የሀገሪቱ ሕዝቦች ዘንድም ተመሳሳይ ችግር ሊከሰት ይችላል በሚል ተግባራዊ ሳያደርጉ የቀረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ይህን እንዲያረጋጋ እና እንዲያስተካክል ኃላፊነት የተሰጠው ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣኑ በድንገት ሞተ መባሉ ብዙ ግምቶችን እንዲሰነዝር እያደረገ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል።

በዚህም መሠረት ወያኔ ከደደቢት በረሃ ጀምሮ የራሷን የቁርጥ ቀን ልጆች ስትቆረጥም እና ስትቀረጥፍ እንደመጣችው ሁሉ በቅርቡ ክንፈ ገ/መድህን በእጅ አዙር አስገድላዋለች ተብሎ በሰፊው ሲወራ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ይህንኑ የደህንነት ባለሥልጣናት በመኪና አደጋ ስም የገደሉት እራሳቸው ወያኔዎች ሳይሆኑ አይቀርም የሚለው ግምት እያየለ መሆኑንና የገደሉት ወያኔዎችም ቢሆኑ በመኪና ግጭት ሳይሆን በጥይት አናቱን መበርቀስ ግድ እንደማይሰጣቸው የከዚህ ቀደም ተግባራቸውን በመጥቀስ የሚናገሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መኖራቸውን ዘገባው ያስረዳል።

በተለይም የደብረዘይት ከተማን ለመገንጠል በሚደረገው ሴራ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ከተባሉት የወያኔ ባለሥልጣናት መካከል አንዱ ይሄው ታሪኩ ሴዶ በመሆኑ ምናልባትም ውልደቱና እድገቱ አዲስ አበባ በመሆኑ በሚደረገው ወያኔያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቀድሞ ሲያደርገው የነበረውን እንቅስቃሴ ባለማድረጉና የመቆርቆር ስሜት በማሳየቱ ሳይሆን እንዳልቀረም ይኸው ዘገባው ያለውን ግምት አክሎ ገልጿል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*ይሁን እንጂ ይህ ግምት ከግምትነት በዘለለ ጠቁዋሚ ፍንጭ አልሰጠም ምክንያቱ ደግሞ የታሪኩ ሴዶን ታማኝነት ያስታክካል*

*ወያኔ ወደ አራት ኪሎ ቤተመንግስት እንደገባ በ1983 ዓ.ም የደህንነት መስሪያ ቤት ተራ ሰራተኛ ሆኖ የጀመረው ታሪኩ ሴዴ በተከታታይ በሚሰራው ወያኔያዊ ተግባሩ እድገት ተሰጥቶት ለ10 ዓመታት የደቡብ ክልል የደህንነት ኃላፊ ሆኖ ሲያገለግል የቆየና በተለይም በአዋሳ ከተማ አቅራቢያ ሎቄ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሕዝቡ በመትረየስ እንዲያልቅ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ከነበረው ሃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በመሆን ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ሲሆን፣ በዚህም ባስመዘገበው የሕዝብ እልቂት እንደ አኩሪ ተግባር ተቆጥሮለት የደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ዳይሬክተር ሃላፊነት እንደተሰጠው የደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።*

*በሃገሪቱ ደህንነት ባለሥልጣን ደረጃ ሶስተኛው ሰው መሆኑን የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ታሪኩ ሴዴ በቅርቡ ደብረዘይትን ወደ ፌዴራል ለማስገባት ወያኔ ባቀደው መሠረት ይህንኑ እንዲተገብር ሥልጣን ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም በተሰጠው ጊዜ አልተጠናቀቀም ተብሎ በወያኔ ባለሥልጣናት ግልምጫና ወቀሳ ሲሰነዘርበት የነበረ መሆኑንና ምናልባትም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሳይገደል እንዳልቀረ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።ሲያልቅ አያምር ይሉት ይህ ነው*

*ያም ሆነ ይህ በደብረዘይት መንገድ በመኪና አደጋ የወያኔ ሰዎች ሲሞቱም ሆነ ሲጋጩና ቆስለው ሲተርፉ ታሪኩ ሴዶ የመጀመሪያም የመጨረሻም አልነበረም ያለው ዘገባ ባለፈው ሳምንት ውስጥም የወያኔው የምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር ዶ/ር መርጋ በቃና የተባለው ግለሰብ ደብዘረይት ከተማ ሲዝናና አምሽቶ ከምሽቱ 4 ሰዓት ወደ ቤቱ በሹፌር በመመለስ ላይ እንዳለ ገና ከከተማው እንደወጣ ከአንድ ቶዮታ ዲ ኤክስ መኪና ከያዘ ሰው ጋር በመጋጨቱ ሰውዬው ወዲያውኑ የሞተ ሲሆን፣ ዶ/ር መርጋ በቃናም በድንጋጤ እራሱን ስቶ ሆስፒታል ገብቶ እንደነበረም ለማወቅ ተችሏል።*

*በወቅቱ የዶ/ሩ ሹፌርም ቃሉን ብቻ ሰጥቶ እንደተለቀቀ ከስፍራው ከነበሩ የአይን እማኞች ለማወቅ ተችሏል።ይህንን የተከታተሉ ነዋሪነታቸው በአዲስ አበባ የሆነ አዛውንት መኪና መኪና እሉ ስለአደጋ የሚነግሩን ማንንለማታለል ነው?ሲባልእንደሚሰማው የደም ግብራቸውን ለማቅረብ ሆን ብለው ጭዳየሚያደርጉትን ሚስጥራቸውን የማያውቅ ያለ ይመስላቸዋል እንዴ ? በማለት በቁጭት መናገራቸው ተመልክቶዋል*



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በእርግጥም የእግዚያብሄርን ለእግዚያብሄር ፣የቄሳርን ለቄሳር እንዲሉ ነውና የወያኔን ለወያኔ የህዝባችን ለህዝባችን፤

ወያኔ ለለመደው የደም ግብር አባላቱንና ራሱን ገብሮ አይኑ እስከሚጠፋ የሚጠብቅ በረሃብ አለንጋ የሚገረፍ ህዝብ ይኖራል ማለት የጨለመው ለሊት አይነጋም ማለት ይሆናልና እነሱም እየተገዳደሉ እኛም ልብ ለልብ ተግባብተን መተባበር አለብን ያሉት ከዚሁ ከታሪኩ ሴዶ መሞት ጋር በተያያዘ አስተያየት ሰጪዎች ናቸው

በየአቅጣጫው በሃገሪቷ ሕዝቦች ላይ ወያኔ ባመጣው ጠንቀኛ ፖሊሲ ምክንያት እና በሚፈፅማቸው የግፍ አገዛዝ ሳቢያ ከፍተኛ ኑሮ ተከስቶ በከፍተኛ ችግር ውስጥ በሚገኙበት ወቅት እንደልቡ የሚያሽከረክረውንና እንደልቡ ጉዳይ የሚያስፈፅሙትን የተካዮች ም/ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቋሚ ሰራተኞች በላንጋኖ ድል ባለ ድግስ እንዲዝናኑ ማደረጉ ታውቋል::

የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ ከመንግስት ካዝና ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ተደርጐ ለእያንዳንዱ የምክር ቤት ሰራተኞችና የፌዴሬሽን ም/ቤት ቋሚ ሰራተኞች የውሎ አበል በሚል አንድ መቶ ሃምሳ ብር በእጃቸው የተሰጠ ከመሆኑም ባሻገር የመጓጓዣ አውቶቡስ በነፃ ማቅረቡንና፣ በዚሁ ወቅት ቢራና ውስኪም እንደ ውሃ ሲከለበስ እንደዋለም አስረድተዋል::

ከ 4 ሰንጋ በላይ ታርደላቸው ላንጋኖ ድረስ ተወስደው ሲጋበዙ የዋሉት የሁለቱም ም/ቤት ቋሚ ሰራተኞች ይህን በመሰለ ጥቅማ ጥቅም እየተሸነገሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል ወያኔ ሲፈፅም አብረው እንዲያጨበጭቡና እንዲያስፈፅሙ ማባበያ መሆኑን የገለፀሉት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ከዚህ ቀደምም ይደረግ የነበረ ቢሆንም የአሁኑ ግን ዝግጅቱ በመጠኑም ሆነ በይዘቱ ሰፋ ያለና ከፍተኛ ወጪ የወጣበት መሆኑንም እነዚሁ ምንጮች ሳይሸሽጉ ገልፀዋል::

ዛሬ የሀገሪቷ ሕዝቦች የዕለት ጉርስ አጥተው ባለበትና ይባስ ብሎም ስግብግቡ ወያኔ ባመጣው ጣጣ የኑሮ ውድነቱ ንሮ ሕዝቡን አላላውስ እያለው የወያኔው ዘረኛ ቡድን ለስልጣኔ እድሜ ያራዝሙልኛል ብሎ ያሰበውን ሁሉ እያደረገ ሲሆን፣ አሁንም የሁለቱን ም/ቤት ሰራተኞች የውሎ አበል ከፍሎ በቢራና ውስኪ አልፎ ተርፎም በጮማ ልባቸውን እያማለለ መገኘቱ ተጋባገሮቹም ከወያኔ ያልተናነሰ ከሀሰተኛ በደል በሕዝብ ላይ እንደፈፀምን ይሰማኛል ሲሉ እነዚሁ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወያኔ የራሱን እድሜ ለመቀጠል ብቻ የሕዝብ ገንዘብ እንደልቡ እየረጨ ከድህነት ወለል በታች የደሀዎች ደሃ ማድረጉ ሳያንሰው መልሶ ባስታጠቀው ቅጥር ወታደሩ እያንገላታው ስለ ኑሮ ውድነቱ እንኩዋን እንዳያወሩ ከአምባገነኑ ደርግ በባሰ መልኩ እጅግ አፋኝ መሆኑን የገለፁት አንድ የዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት መምህር በአሁን ወቅት ግን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አደገኛ አጣብቂኝ ውስጥ መግባታችንን ያረጋገጥንበት ወቅት ላይ ደርሰናል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

አክለውም ዛሬ የሀገሪቱ አዝቦች በኑሮ ውድነቱ መካበድ የተነሳ መሽከም አቅቷቸው እየተንገዳገዱ ባለበት ወቅት ከመንግስት ካዝና እንደልብ እየመረጡ አንዴ ደደቢት፣ ሌላ ጊዜ ሽሬ እንደስላሴ አስረሽ ምችው እያሉ ከርመው እንደገና እንደልባቸው ለሚልኩዋቸው ቡችሎቻቸው ከፍተኛ መጠን ያለው የሕዝብ ገንዘብ ወጪ አድርገው ሲዝናኑ መስንበታቸው በእጅጉ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ከመሆኑም ባሻገር ሕሊናን የሚያቆስል ድርጊት ነው ሲሉ እልህና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወያኔዎች በሕዝቡ ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ ከጀመሩ 16 ዓመታትን ያስቆጠሩ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ግን መውሰድ የጀመሩት የበቀል እርምጃ ረቀቅ እያለ መምጣቱን የሚሳያዩ ምልክቶች መኖራቸውን መታየቱ ተጋለጠ፡፡

ሰሞኑን የአቃቂ ምግብ ማደራጃ የተባለው የምግብ ፋብሪካ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑና የተበላሹ ምግቦችን በጨረታ ለመሸጥ መዘጋጀታቸውን ከወጣው ማስታወቂያ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የተበላሹ እና የአገልግሎት ዘመናቸው የተበላሽባቸው ምግቦችን በጨረታ እንሸጣለን በማለት ባፈጠጠና ባገጠጠ መልኩ ለሕዝብ ይፋ መደረጉ ወያኔ ከመቼውም ጊዜ በላይ በሕዝቡ ላይ እየወሰደ ያለውን የበቀል እርምጃ እያጠናከረና እየሰፋ መሄዱን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

በተለይም የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው የምግብ አይነቶች ጉድጓድ ውስጥ ሊቀበሩ ወይም ሊቃጠሉ ሲገባ በጨረታ መልሶ ለህዝቡ በይፋ ማቅረቡ ሕዝቡ የተበላሸውንና የተመረዘውን ምግብ በልቶ እንዲያልቅ ለማድረግ የታሰበ መሆኑን በቁጭት የሚገልፁት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፋሽት ጣሊያን ከዚህ በላይ ምን ሰራ ብለን ልንወነጅለው ይቻለናል? በማለት በንዴት መግለጻቸው ተዘግቦዋል ፡፡

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ በቀን አንድ ጊዜ መብላት የተሳናቸው ዜጐች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጥቶ ሁሉንም ሕዝቦች ሊያዳርስ በተቃረበበት በዚህ ወቅት ወያኔዎች ፍቅረ ንዋይ ያላቸው በመሆኑና ሕዝቡን ስለማይፈልጉት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የተበላሸ ምግብ ለመቸብቸብ ይፋ ጨረታ ማውጣታቸው ሕዝቡን ንቀውት እንደሆነ በተጨባጭ የሚያስረዳ ነው ሲሉ እነኚሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በቁጭት ይገልፃሉ፡፡

በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የወያኔው ቡድን «የፀረ ሰላም ኃይል ደጋፊ ናችሁ» እያለ የጅጅጋን ሕዝብ የቁም ስቅል እያሳየ መሆኑን ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ አጋለጠ፡፡

የወያኔ ቡድን ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ከተባለው ታጣቂ ኃይል ጋር ውጊያ መግጠሙንና ሙሉ በሙሉ ነፃ አውጥቻለሁ እያለ ቢለፍፍም ግንባሩ ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሱም በላይ በተጨማሪ በርካታ የጦር መሣሪያ እየማረከ መሆኑ እየተነገረ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ካድሬዎች በጅጅጋ ከተማ ያሉትን ሕዝቦች «የግንባሩ ደጋፊዎች ናችሁ፣ በውስጣችሁ ሸሽጋችኋል . . .» በማለት ሰላማዊ ነዋሪችን የቁም ስቅል እያሳይዋቸው መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

በመከላከያ ጦር፣ በፌዴራል ፖሊስ፣ በካድሬዎችና በደህንነት ኃይሎች የስንግ የተያዘው የጅጅጋ ሕዝብ በሠላም ሰርቶ እንዳይበላ እየተደረገ ሲሆን፣ ከከተማው ለመውጣት ካለባቸው ስጋትና ፍርሀት የተነሳ በርካታ ተነቃናቂ ነጋዴዎች ስራቸውን አቁመው ለመቀመጥ መገደዳቸውን ይኸው ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

በከተማዋ የሚኖሩ የክልሉ ተወላጅ የመንግስት ሰራተኞችም በገቡና በወጡ ቁጥር ሁለትና ሶስት ሆነው ከታዩ በደህንነት ኃይሎች ክትትል እየተደረገባቸው እንግልትና ወከባ የሚደርስባቸው ሲሆን በድርጊቱ ከመማረራቸውም የተነሳ አንዳንድ በጭንቀት በመታመም ላይ መሆናቸውንም ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

በቅርቡ ግንባሩ ከፍተኛ ሽንፈት የደረሰበት የወያኔው ቡድን በወሰደው አፀፋዊ እርምጃ በጦር ሂሊኮፕተርና ጄት ጭምር ንፁሀን ዜጐች ላይ ያለ አንዳች ርህራሄ ጭፍጨፋ ማድረሱ የተዘገበ ሲሆን፣ ቤትና ንብረቶቻቸው ጋይተው እግሬ አውጭኝ ብለው ወዳገኙበት ቦታ በማምለጥ ለጊዜው ሕይታቸውን ያተረፉ ዜጎች ቢኖሩም አረመኔው ወያኔ ለእነዚህ ዜጐች ምንም አይነት የውሃና የምግብ እርዳታ እንዳይደርሳቸው ለጋሽ ድርጅቶችን ሁሉ በማገድ ለብዙ ቀናት በረሀብ ሲቆላቸው እንደነበር ያወሳው ይኸው ዘገባ በወያኔ ቦምብ ድብደባ አካላቸው



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የተቆረጡት ንፁሃን ዜጐች ጅጅጋ ዘመዶቻቸው ጋር መቀላቀላቸውንና በቅርቡ ደግሞ እነዚሁኑ ተጎጂዎች በጅምላ አፍሶ ሊወስዳቸው መሆኑንም ጨምሮ ገልጿል::

የወያኔው አረመኔ ቡድን እራሱ በፈፀመው ዘግናኝ የግፍ ተግባር አካላቸውን አጥተው በጅጅጋ ከተማ ዘመዶቻቸው ጋር የተቀመጡትን ንፁሃን ዜጐች መልሶ እዚህ ለምን ተቀመጡ? በአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ያጋልጡኛል በሚል ስጋት ብቻ አፍሶ ወዳልታወቀ ስፍራ ሊወስዳቸው ዝግጅት ማጠናቀቁን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

የጅጅጋን ከተማ ነዋሪዎች «አሸባሪዎችን አጋልጡ» በሚል ነጋ ጠባ በየቀበሌው ስብሰባ እያለ ሕዝቡን ከማሰልቸታቸውም በተጨማሪ እያንገላቱና እያሰቃዩት መሆኑንም ይኸው ዘገባ አጋልጧል::

የሻዕቢያ ቡድንና አንሚ በመወዛገብ ላይ ሲሆኑ ወያኔ ደግሞ ጦሩን እያጠናከረ እንደሚገኝ ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::

ሰሞኑን የወያኔ መከላከያ መስሪያ ቤት ውስጥ የውጭ ሀገር ዜጐች መኮንኖች እንደታዩና ከፊሎቹ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማን ለመጐብኘት ሲዘዋወሩ እንደሰነበቱ ምንጮች ገልፀዋል::

ዜግነታቸው የየት ሀገር እንደሆኑ በትክክል ያልታወቀው እነዚህ የውጭ ሃገር ሰዎች በመከላከያ ሚኒስተር ቢሮ ውስጥ ወታደራዊ ካርታ ተሰጥቷቸው ሲያነቡና የወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችን ሰብስበው በካርታው ዙሪያ ሲያነጋግራቸው እንደነበር የገለፁት ምንጮቹ በተለይም በአሁን ሰዓት ወያኔ በሰሜን ከሻዕቢያ ጋር ተፋጥጦ ባለበትና በምስራቅም ከተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች ጋር እየተፋለመ ባለበት በዚህ ወቅት በዚሁ ችግር ዙሪያ መፍትሄ እንዲሰጡ አማካሪ ሆነው የመጡ ሳይሆኑ እንደልቀሩ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል:::

የወያኔ ቡድን ከበረሃ ይዟቸው በመጣው የሕወሓት ጄኔራሎች ባለመተማመኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸውን ከፍተኛ ጄኔራሎች በከፍተኛ ክፍያ ለአማካሪነት ያመጣቸው ሲሆን እነዚህ አማካሪዎች የአሜሪካ ወይም የራሺያ ዜግነት ያላቸው መኮንኖች ሳይሆኑ እንደማይቀሩም ምንጮቹ ገልፀዋል::

የወያኔው ቡድን ደደቢት የተወለደበትን በዓል ባከበረ ሰሞን በድብቅ ቦታ አዲስ አበባ ውስጥ አስቀምጦት የነበረውን ሚሳኤል ባለፈው ሳምንት ወደ ግንባር ያጓጓዘ ሲሆን፣ ምናልባትም እነዚህ የውጭ ሀገር ዜጐች ከዚሁ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሚሳኤል ጋር አብረው የመጡ ሳይሆን እንደልቀረ ያስቀመጣቸው የወያኔ ተላላኪ መኮንኖች ስለካርታም ሆነ ስለሚሳኤል የጠለቀ እውቀት ስለሌላቸው ሳይወድ በግዱ በከፍተኛ ክፍያ ሊያስመጣቸው እንደቻለም ምንጮቹ አስረድተዋል::

ዛሬ ተነሳ ነገ ይፈነዳል እየተባለ በከፍተኛ ፍጥጫ ውስጥ ያሉት ወያኔና ሻዕቢያ ከሕዝባቸው ጉሮሮ ላይ እየነጠቁ ከፍተኛ የጦር መሣሪያዎችን እየታጠቁ መሆኑ ሁለቱም ቡድኖች በስልጣን ላይ ለመቆየት ካላቸው ምኞት የተነሳ መሆኑን ያሳያል ያሉት አንድ የቀድሞ መኮንን ናቸው

እኒሁ የቀድሞመኮንን በተለይም ወያኔ በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የኑሮ ወድነት በህዝቡ ላይ እያናጠረ ባለበት በዚህ ወቅት በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ በማድረግ ሚሳኤል መግዛቱ ሳያንሰው እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወጪ በማድረግ የውጭ ሃገር ለአማካሪነት ማስመጣቱ በጣም የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፀዋል::

የወያኔ ቡድን በሰሜን በኩል እንደብራና ተወጥሮ ባለበት ወቅት የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ነኝ ብሎ የሚታገለው ቡድን ጋር ባለፈው ሳምንት ውጊያ ማድረጉ ደግሞ ለወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች ሌላ አዲስ የራስ ምታት እንደሆነባቸው በወቅቱ በውጊያው ድንገተኛ ጥቃት የተሰነዘረባቸው በመሆኑ የተነሳ ከባድ ጉዳት ሳይደርስ እንዳልቀረ የገለፁት የመከላከያ ምንጮቻችን አሁንም በመከላከያ ሚኒስተር ግቢ ውስጥ ምክንያቱ ያልታወቀ ትርምስ እንዳለ ገልፀዋል::

በተመሳሳይ መልኩ በአየር ኃይል ግቢ ደብዘረይት በርካታ የውጭ ሀገር የአየር ኃይል ባለሙያዎች እንዳሉ የገለፁት ምንጮቹ እንደ እግረኛዉና የሚሳኤል ባለሙያዎቹ ለአየር ኃይሉም ካርታ ለማንበብና ለማሳየት ይረዳሉ ተብሎ በከፍተኛ ዋጋ ኮንትራት ተዋውለው ሳይመጡ እንዳልቀሩ ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

የወያኔው ዘረኛ ቡድን በሰሜንና በምስራቅ ፋታ የነሳው ጦርነት ውስጥ ተዘፍቆ ባለበት በዚህ ሰዓት በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ረብሻ እንዲነሳ ካደረገ በኋላ ሁለት ተማሪዎች እንደተገደሉ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ባለፈው ሳምንት የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔ ቡድን ደደቢት የተወለደበትን 33ኛ ዓመት በዓል በሽሬ እንደስላሴ እያከበረ ባለበት እለት በዲላ ዩኒቨርስቲ በተማሪዎች መካከል ግጭት እንዲነሳ ሆን ተብሎ በተደረገው ምክንያት ነገሩን ለማብረድ በሚል ሰበብ በከተማዋ ሰፍሮ የሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ ግቢ ገብቶ ተማሪዎቹን በመሣሪያ ኃይል እያስፈራራ በብረት ዱላና በጣውላ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበደባቸው ሲሆን፣ ለጊዜው ስማቸው ያልታወቁ ተማሪዎች ሕይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

ወያኔ ብሔርን ከብሔር፣ ኃይማኖትን ከኃይማኖት ለማጋጨት ቢሞክርም አልሳካ ያለው ቢሆንም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝብን ከሕዝብ እያጋጨ እርስ በእርስ እንዲተላለቁ እያደረገ ሲሆን፣ ለዚህም በቅርቡ በደቡብ ውስጥ መታየቱና ፣ አሁንም በዲላ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ይህን የመሰለ ዘግናኝ እርምጃ በፌዴራል ፖሊስ እንዲወሰድ ማድረጉ ወያኔ ያለውን ድብቅ ባህሪ ጉልቶ ያወጣበት አጋጣሚ ነው ሲሉ የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ አባላት መናገራቸውን የደረሰን ዘገባ አክሎ ገልጿል፡፡

በአሁን ሰዓትም የዲላ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ተቋርጦ ያለ ሲሆን፣ በርካታ ተማሪዎች በድብደባው የተጎዱ በመሆኑ ግማሾቹ በዶርማቸው ውስጥ የተኙ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ወደ ቤተሰቦቻቸው እንደሄዱም ዘገባው ጨምሮ አስረድቷል፡፡

በተመሳሳይ የአራት ኪሎ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች በድጋሚ አሁንም ተቃውሞ ማሰማት ጀመሩ፡፡

ከዚሁ ቀደም ተደጋጋሚ በሆኑ ቀናቶች ውስጥ የሕዝብ አድማ አድርገው ተቃውሟቸውን ያሰሙ ሲሆን፣ ሲርባቸው ይበላሉ ተዋቸው በማለት የአዲግራቱ ተወላጅ አባ ጢሞቲዎስ እንኳዋንስ መንፈሳዊ ክፉ ተባለ እንጀራ አባት በማያደርገው ሁኔታ ቢገልፁም አሁንም ተማሪዎቹ የሚያነሱት ጥያቄ ጭብጥ የለውም በማለት በማጣጣል ላይ እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

ተማሪዎቹ በእኛ ስም ከተለያዩ ሃገራት እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እየገባ ነው ይሁን እንጂ ገንዘቡ የት ገባ? የምንመገበው ደረጃውን የጠበቀ አይደለም፡፡ በኮሌጁ ውስጥ አድልኦ ሙስና ተንሰራፍቷል? አባ ጢሞቲዎስ እኛን መምራት አይችሉም የትምህርት ደረጃቸው አይፈቅድላቸውም የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች አንስተው የነበረ ሲሆን አሁንም ተማሪዎቹ ያነሱት ጥያቄ ምላሽ ባለመግኘቱ ተቃውሞ ዳግም መጀመሩን ከአይን እማኞች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተለይም ለአባ ገ/መድህን ቅርበት ያላቸው አባ ጢሞቴዎስ ባላቸው ቀረቤታ የሚኩሩና ተማሪዎቹን ለማነጋገር እንኳዋን የማይፈልጉ መንፈሳዊ አባት ሳይሆኑ ክፉ እንጀራ አባት የሆኑ ግለሰብ መሆናችን ብዙዎች ይስማሙብታል

አሁንም መጀመሪያ ትልልቅና የተማረ የሰው ኃይል ይቀመጥበት በማለት ተማሪዎቹ ተቃውሟቸውን ማሰማት ጀምረዋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በዚህም ምክንያት የተነሳ የአራት ኪሎ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለማቆም የተገደዱ ሲሆን የውሃ እጥረት ስላጋጠማቸው በውሃ እጦት እየተሰቃዩ መሆኑንም ጨምረው ሲገልፁ መደመጡን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com